# ''ጸረ ለውጥ '' ቡድኑ ተሳካለት ወይስ ''ለውጡ'' ጭምብል ነበር?

''ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መቀንጠሷ'' አሉ አበው ሲተርቱ ሁኔታዎችን በፍጥነት መላመድ ያለውን አደገኝነት በምሳሌያዊ ዘይቤ አጣፍጠው ሲናገሩት ማለት ነው። '' የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳልም '' ይላሉ። ስጋ አገኘሁ ብሎ መወጊያውን ይነካል እንደማለት ነው። '' የቸኮለች ደፍታ ለቀመችም'' ይባላል። ከላይ የጠቀስናቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች በሙሉ ተመሳሳይ ነገሮችን ለመግለጽ የሚያገለግሉ ናቸው። '' ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው '' በማለት መላ አገር አፍቃሪውን ያስፈነጠዙት አቶ ለማ የስነ ልቦና ሰለባ መሆኑን የገመተ ይኖራል ብየ ፈጽሞ አላስብም። ኢትዮጵያ ማለት ተራ ነገር አይደለም፣ ኢትዮጵያዊነት ምስጢር ነው በማለትም አበባላቸውን አብራሩት። **በቅጽበት አልጋ ወራሻቸው እንዲሆኑ ዶክተር አብይን ለኦህዴድ ሊቀመንበርነት ወደ ፊት ሲያመጧቸውም እኝህ ሰው ስልጣን ሳይሆን ፍትህን ነው የተጠሙት በማለት የአድናቆት ጎርፍ ተዥጎደጎደላቸው።** ዶክተር አብይም '' አቶ ለማ በፊት በግልጽ አሁን ደግሞ በምስጢር አማካሪየ ነው '' ሲሉም በአደባባይ ነገሩን። በሌላ መንገድ ዶክተር አብይ አገሪቱን ከአቶ ለማ ጋር እንደሚመሯት እየነገሩን ነው።'' አያ በሬ ሆይ ገደሉን ሳታይ'' እንዲሉ ላለፉት ሰስት አስር አመታት የተጠማነውን'' ኢትዮጵያ '' የሚል ቃል በአንድ ሳምንት ሲያዥጎደጉዱልን ከጀርባቸው ሴራና ተንኮል ይኖራል ብለን መገመት ፈጽሞ አልቻልንም ነበር። ወያኔ በተለይም አንድን ማህበረሰብ ጠላቴ ብሎ ፈርጆ እድገቱንም ስርቆቱንም ሲያጧጡፈው ስለሰለቸን ፣ አገራዊ አንድነትን በመከፋፈሉ ዜጎች በሄዱበት ሁሉ በሰላም መኖር አለመቻላቸውና በገዛ አገራቸው መፈናቀልና መገደላቸው ከሙብዛቱ የተነሳ የወያኔን ጠላት ሁሉ ወዳጅ ማድረግ መፍትሄ መስሎ የታየን ብዙዎች ነበር።ነገር ግን ምንም እንኳ ለመስማት **ብንቸገርም የጠላቴ ጠላት ሁሉ ወዳጄ ሊሆን አይችልም** ብለው የመከሩን አልታጡም ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ዶክተር አብይን በግል ስብዕናው የምናውቀው ሰዎች ነገሮችን በብልጠት ከማድረግ ውጪ በጎሳዊ ስሜት ዘቅጦ የገኛል ብለን አንጠረጥርም ነበር ፤ አሁንም የአቅም ጉዳይ ሆኖበት እንጂ ዘረኛ ሆኖ አይደለም የሚሉ ሰዎች መኖራቸው ይታወቃል። ነገር ግን በዐማራና በትግራይ መካከል ያለው ግጭት ለመባባሱና አጭርና አፋጣኝ ምላሽ የማይሰጥበት ምክንያት ግልጽ ያልሆነልን ዜጎች ጥልቀት ያለው ጥናት እንድናጠናና መሰረቱንም እንድንረዳ ወቅቱ ያደረገን ይመስላል። ዶክተር አብይ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ እያለ ጎሳውን ለምን ይጠቅማል? የሚል የደደብ ጥያቄ አልጠይቅም ። ጥያቄየ አድሎአዊ አሰራር ለምን ይሰራል ? ነው። **ወያኔ ይህንን አጠፋ ወያኔ ያንን አደረገ በማለት ስለ ትናንት እየተረክን እንድንኖርስ ለምን ተፈለገ?** የአድሌሪያን ሳይኮሎጂ( Adlerian psychology) አባት የሆነው አልፍሬድ አድለር '' "No experience is in itself a cause of success or failure," he wrote in his 1931 book, *What Life Could Mean to You.* "We are not determined by our experiences, but are *self-determined* by the meaning we give to them; and when we take particular experiences as the basis for our future life, we are almost certain to be misguided to some degree. Meanings are not determined by situations. We determine ourselves by the meanings we ascribe to situations."

እንደሚከተለው ተርጉሜዋለሁ። እ ኤ አ በ1931 ዓ ም '' *What Life Could Mean to You" በሚል ርእስ በጻፈው መጽሃፉ ''* ምንም አይነት ያለፈ ልምምዳችን ለስኬታችን ወይም ውድቀታችን ምክንያት መሆን አይችልም፤ ባሳለፍነው ልምምድ አንወሰንም ፤ የምንወሰነው ለልምምዶቻችን ራሳችን በምንሰጠው ትርጉም ነው ፤ አንድን የተወሰነ ልምምድ ለወደፊት መነሻችን ወይም መሰረት የምናደርገው ከሆነ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እንደሚመራን በእርግጠኝነት ማዎቅ ይኖርብናል። ትርጉም በሁኔታዎች መመስረት የለበትም። ራሳችንን የምንወስነው ለሁኔታዎች በምንሰጠው ትርጉም ነው።'' በማለት ይናገራል። ዋና ሃሳቡ ዛሬን በዛሬነቱ በመቀበል ወደፊት መጓዝ እንደሚገባ ሁሉን ነገር በዛሬና በአሁን መነጽር በማየት በአላማ መኖር እንዳለብን የሚያስገነዝብ ቲዮሪ ነው። በእርግጥ የዚህ ስነልቦና ተቃዋሚዎችም ደጋፊዎችም አሉት። እኔ እዚህ ያነሳሁት ግን በሃገራችን ፖለቲካ **ትናንት በሆነው እየተፋጨን ፣ ትናንትን ለዛሬያችን ችግር ምክንያት እያደረግን ጊዜያችንን እንድናቃጥል እየተሰራ መሆኑን ለመጠቆም ብቻ ነው።** ወያኔ ትናንት ላጠፋው ከቻልን ፍትህ በህጋዊ መንገድ እንዲገኝ የበኩላችንን ጥረት በማድረግ ዛሬንና ነገን እንዳይነካብን ማድረግ እንጂ ትናንት ወያኔ ይህንንና ያንን አድርጓል

በማልት ጊዜያችንን ማጥፋት ሌላ አረንቋ ውስጥ መግባት ነው። ወያኔም ዛሬ እያደረገው ባለው ሴራም ሆነ ተንኮል መታገል እንጂ በትናንትናና በሞተ ድርጊት በመከራከር ጊዜ ማጥፋት ጉዳት ነው። **ዶክተር አብይን የምንቃወመውም ሆነ የምንተቸውም ትናንት ለምን ፊንፊኔ የኦሮሚያ ነች አለ ብለን ሳይሆን ዛሬ ኢትዮጵያውያን እንዲጋጩ ፣ እንዲጋደሉና ባልሆነ የይገባኛል ጉንጭ አልፋ ክርክር እንዲገቡ ለምን አደረጉ? ነው።** ዶክተር አብይ እንደሚናገሩት ፍትህን በአገሪቱ እያሰፈኑ ለእኩልነትና ዲሞክራሲም ከልባቸው እየሰሩ እንዳልሆነ የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል።

በአስተዋይነቱ ወደር የሌለው የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ታግሷቸው ነበር። የጭቆና ቀንበር ያንገሸገሻቸው ከጫፍ ጫፍ ህይወታቸውንና ደማቸውን ያፈሰሱ ኢትዮጵያውያን መጣ ለተባለው ለውጥ ግንባር ቀደም ተጠቃሾች መሆን ሲገባቸው ለውጡ የመጣው በአንድ ቡድን ነው ተብሎ ከሚገባ በላይ ተለጠጠ። በዚያው በራሱ በኢህዐዴግ ውስጥ የነበሩ  ፍትህና ነጻነት የጠማቸው በርካታ ዜጎች የማይደፈር እየደፈሩ ሲናገሩ ራሳቸውን ለሞት ለመስጠት ወስነው በውስጣችን ጭቆና አለ በማለት ሲሞግቱ ቀድመን ብንሰማም የለማ ቡድን የሚባል መለኮታዊ ሃይል ነው ተባለና ሌሎች ተርሱ። አድሎአዊነት  ከዚህ ይጀምራል። ለመሆኑ  በብአዴን ስብሰባ ላይ ሸንጡን ገትሮ እነ በረከትና ህላዊ ዮሴፍን  እናንተ ተላላኪ ናችሁ፤ የዐማራን ጥቅም አታስከብሩም ብሎ የሞገታቸው ወጣት አሁን የት አለ? በራሳቸው በኢህአዴግ ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስቴርነት ህጋዊ መብቱ ሆኖ እያለ ሌሎች ይሻላሉ በማለት ራሱን ዞር ያደረገው ደመቀ መኮነን በየትኛውም አጋጣሚ ሲዘመርለት አልሰማንም ። ነገር ግን ዛሬ በአዲስ አበባ ለኦሮሞ ጥቅም ጉዳይ አንደራደርም በማለት አወዛጋቢ የሆነ መግለጫ የሚሰጡት ለማ የለውጥ ሃዋርያ ተባሉ።

ለማ አንድ ሚሊየን አካባቢ የሚጠጉት የጊድዮ  ተፈናቃዮች ሳይሆኑ የሚያስጨንቃቸው የፊንፍኔን ዲሞግራፊ የመቀየሩ ጉዳይ ሆኗል። ስለዚህም ሌላው ኢትዮጵያዊ ለእርሳቸው ኦሮሞ ወደ ከተሞች እንዲፈልስ  መንገድ መሆን ብቻ እንጂ ለማኝ ወይም ጎዳና ተዳዳሪ መሆኑ አያሳስባቸውም። **ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው በማለት ቀልቡን የነጠቁት ኢትዮጵያዊ ድራማ ማየት ስራው ሆኗል**።

ዐማራና ትግራይ የተባሉት አጎራባች ክልሎች እንዲጋጩ በመካከላቸው ያለው መናቆርም መቆም እንዳይችል ተደርጎ የተሰራበቱ ምክንያት አሁን በግልጽ እየታየ ነው። የወልቃይት የዐማራ ማንነት ጥያቄም ሆነ የራያ ማንነት ጥያቄ የተወለደው ራሱ ኢህአዴግ በሚከተለው ዘር ተኮር ርዕዮተ አለም መሆኑ እየታወቀ ታድሻለሁ ያለውና ራሱን የለውጥ አመራር በማለት የሚጠራው ቡድን ትኩረቱን የነፈገው ሆን ብሎ የሁለቱ ክልል ህዝቦች እንዳይረጋጉ ለማድረግ መሆኑ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ አሁን ተገልጧል። በዐማራና በትግራይ ህዝብ መካከል ምንም አይነት ቂም ወይም ቁርሾ ያለመኖሩ ማረጋገጫ  በመለስና ግብረ አበሮቹ  በተሰራው ደባ ኤርትራውያን የዘላለም ጠላቶቻችን ተደርገው ቢሳሉም በቅርብ የኤርትራው ፕሬዚደንት ኢሳያስ አፎርቂ ኢትዮጵያን ብሎም የዐማራ ክልልን ሲጎበኙ ህዝብ የፕሬዚደንቱ ማንነት ሳይበግረው ለኤርትራውያን ያልውን ክብር የገለጸበት መንገድ ግልጽ ነበር። ዛሬም ፖለቲከኞች በፈልጋቸው መንገድ ጠላትነትን በትግራይ ህዝብና በዐማራ ህዝብ መካከል ሊያደርጉ ቢሞክሩም የተደበቀ ሳይገለጥ የሚቀር እውነት የለም። የኦሮሞ ጽንፈኞች ስልጣን በእጃችን ነው ምንስ ታደርጉናላችሁ በማለት በመደንፋት ላይ ይገኛሉ። ቢፈልጉ አዲስ አበባ የኦሮሞ ነው ማንም አያገባውም በማለት የባለቤትነት መብቱ የራሳቸው ብቻ እንደሆነ ይሰብካሉ። ይህ  የማያዋጣ ሲመስላቸው ደግሞ  በአዲስ አበባ ዙሪያ በኦሮሞ መሬት ላይ የተገነባው ህንጻ የኦሮሞ ስለሆነ አዲስ አበባ ማከፋፍል አይችልም በማለት ቄሮ የተባለው የጃዋር ታዛዥ ቡድን ሰላማዊ ሰልፍ እንዲወጣ ያደርጋሉ። ህዝብን ለማሸበር ያለፈውን ሃያ ሰባት አመታት ወያኔ የተጠቀመበትን ስልት ዛሬ ደግሞ የአቶ ለማ ቡድን የኢትዮጵያውያንን የተረጋጋ ህይወት በነውጥ ለመምራት እየሞከሩ ይገኛሉ። አቶ ለማ ከወራት በፊት የለውጡ ተቃዋሚወች በብዙ ቦት ብጥብጥ እንዲነሳ እየሰሩ ነው። በተለይም ዐማራውንና ኦሮሞውን ለማጋጨት ይጥራሉ በማለት ሲናገሩ አምነናቸው ነበር። ዶክተር አብይም በሄዱበት ሁሉ ገናናዋን ኢትዮጵያን እንገነባለን በማለት ሲደሰኩሩ ምስኪኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ህይወቱን አሳልፎ እንደ ሚሰጣቸው አረጋግጧል።  አቶ ለማም ሆኑ ዶክተር አብይ ዜጎችን ያሰቃየው አገራችን በዘርና በጎሳ ተከፋፍላ ከእድገት ይልቅ ስለ ግጭት እንዲያስብ ምክንያት  ከሆነው ከዘረኛው ፓርቲ እንደመጡ ቢታወቅም ለሰላም እኩልነትና ፍትህ ሲባል ተቀባይነት ተችሯቸው ነበር።ስለዚህም ኦነግ እዚህም እዚያም ጠብ ያለሽ በዳቦ ሲል ፣ የአገሪቱ  ሃብት የሆኑትን በርካታ

ባንኮች ሲዘርፍ ፣ ንጹሃንን ሲያፈናቅልና ሲገድል ህዝቡ አቶ ለማንና ዶክተር አብይን ላለማሰናከል በሚል ሆዴ ቻለው ሲል ቆይቷል። ኦነግ በሰው ልጆች ላይ የፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀል እያለ ስለፍትህና እኩልነት በሰላም ይታገላል ብሎ ማለም የማይቻል ቢሆንም ያለፈውን በደሉን ለመቁጠር ጣት የሰነዘረበት አልነበረም። ነገር ግን ዛሬም ኦሮሞ ይኖርባቸዋል በተባሉ አካባቢዎች ሁሉ ሌላውን ኢትዮጵያዊ ማፈናቀልና የእኔን ለቀህ ውጣ ማለትን በሰፊው ተያይዞታል። በዚህ አገር ሁለት መንግስት ነው ያለው አንደኛውን እኔ እመራዋለሁ ፣ ቄሮ ይባላል ፣ ከፈለግሁ አሁኑኑ ኦሮሚያን መገንጠል እችላለሁ በማለት በድፍረት እየተናገረ በነጻነት የሚኖረውን ጃዋርን  አቶ ለማም ሆኑ ዶክተር አብይ አንዳችም ቃል  ሊያወጡበት አልፈልጉም። ምክንያቱም ለእነዚህ ሁለት ፖለቲከኞች ኢትዮጵያ  ማለት መዋቅራቸውን በሃገሪቱ እስኪዘረጉ ማስካቸው ነበርና ማለት ይቻላል ። ታከለ ኡማን ከንቲባ አድርጎ አስቀምጦ የፈለገውን እንዲያደርግ ፈቅዶ ያም አላረካ ሲላቸው አዲስ አበባ  በኦሮሚያ መሬት ላይ መወሰን አይችልም እንዲሁም የሰራውን ኮንዶሚኒየም ማከፋፈል አይችልም ብሎ መግለጫ ማውጣት ህዝብን ከመናቅ የመነጨ ነው።በኢትዮጵያ የዘረኛውን የህወሃት አገዛዝ ለጊዜውም ቢሆን ከመድረክ ዘር እንዲል ከፍተኛ መስዋትነት የከፈሉት የዐማራ ወጣቶችና የህዝበ ሙስሊሙ  እንቅስቃሴ ቢሆኑም ጨኸቴን ቀሙኝ ሆነ። የዐማራ ወጣቶች መስዋእትነት ከፍለናልና በኢህጋዊ ሁኔታ መብቱን የተገፈፈው በናዝሬት፣ በደብረዘይት፣ በሃረር፣ በድሬዳውዋ በጅማ፣ በጎባ፣ በአሰላና በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች የሚኖረው የዐማራ መብት ዛሬውኑ  ይከበር፣ ያ ካልሆነ አገር እናፈርሳለን  በማለት ሱሪ በአንገቴ አላሉም። ለውጥ ሂደት መሆኑን በመገንዘብ ለአገዛዙ  ጊዜ ሲሰጡ  አስተዋይነታቸው በተሞገሰ ነበር።  ደማቸውንና ህይወታቸውን በመገበር የኦሮሞ ደም የእኛም ደም ነው በማለት ጎንደር ላይ የጮሁት የአማራ ወጣቶች እኛን ያገለለ ህገ መንግስት በመሆኑ ዛሬውኑ መታገድ  አለበት በማለት ዶክተር አብይን ፋታ የማይሰጥ ጥያቄ አላቀረቡም። ይህም ሁሉን የሚቀበሉ  ንቃተ ህሊና የጎደላቸው እንደሆኑ በማሰብ ዝም ተብሎ ንጹሃን ከሚበሉትና ከልጆቻቸው አፍ ቆጥበው ላሰሩት የጋራ መኖሪያ ህንጻ ለእኔ ጎሳ ካልሆነ  አገር ይፈርሳል ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣቱ ሳያንስ ልክ ነው ይህ መኖሪያ ህንጻ ለኦሮሞ ነው በማለት መግለጫ የሚያውጣ ቡድን በእርግጥ የለውጥ ሃይል ነበረን?

ህዝበ ሙስሊሙም ቢሆን ይህንን አብዮት ያመጣሁት ለራሴ መብት በከፈልኩት መስዋእትነት ነው። ስለዚህም በአንድ ሌሊት ከመንግስት ጋር በመመሳጠር ሲያሳድዱኝ የኖሩ ሁሉ ቤተ እምነቴን ለቀው ይውጡ በማለት ከፋፋይ ሂደት አልተከተለም። **የእነ አቶ ለማ ቡድን ግን ማለቴ የዶክተር አብይ ፓርቲ ግን ማለቴ ቄሮ የመራው አብዮት ግን ማለቴ ጃዋር መሃመድ የሚያዝዘው አገር ተረካቢ ግን ማለቴ የእነ ዳውድ ኢብሳ ኦነግ ግን ለውጥ ያመጣሁ እኔ በመሆኔ አዲስ አበባ የእኔ ነች፣ ኮንዶምኔም መከፋፈል ያለበት ለኦሮሞ ብቻ ነው፣ አዛዥ ናዛዥ እኔ ነኝ፣ መታወቂያም ሆነ ሌሎች ግባቶችን በአዲስ አበባ ለጎሳየ አባላት ብቻ እሰጣለሁ ያ ካልሆነ ግን አገር አፈርሳለሁ በማለት እርምጃውን ቀጥሏል።**

አሁን የትግራይ ህዝብና የዐማራ ህዝብ ብቻ ሳይሆን አገር ወዳዱ ኢትዮጵያዊ ሁሉ መተባበር መደራጀትና ዘረኛውን ቡድን በቃህ ሊለው ይገባል። የትግራይ ህዝብም ሆነ የአማራ ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ ተደራድሮ አያውቅም። ደቡቡ ፣ ኦሮሞው ሶማሊያው አፋሩ ቤንሻንጉሉ፣ ጋምቤላው፣ ሲዳማው፣ ጋሞው፣ጎፋው፣ ወላይታው ጉራጌውና ሌላውም ኢትዮጵያዊ የጋራ አገር እንጂ የኦሮሞ ፣ የትግራይ ፣ የዐማራ ወዘተ የሚባል ደሴት እንደሌለ በመረዳት ለእነ ዶክተር አብይ የሰጠውን እምነት የሚጠራጠርበት ጊዜ ላይ ይገኛል። **ኢትዮጵያችን እምነቱን ለበላ ሲኦል ነች። ጎሰኞች ሊያሸንፉ አይችሉም። ግፍን የመሸከም ጫንቃው ሰፊ የሆነ ህዝብ ያላት ኢትዮጵያ ግፍ በቃኝ ሲልም አንዴ ነው። አዲስ አበባ የበዛ ትእግስቷ የተሟጠጠ ይመስላል።** ትናንት ተለይቶ ሲሳደድና ሲገደል የኖረው የዐማራ ህዝብ ዛሬም አገር ወዳዱን ኢትዮጵያዊ ይዞ ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲና ለእኩልነት መታገሉን እንደሚቀጥል ምንም ጥርጥር የለውም። አቢዮት ልጆቿን ትበላለች፤ የዚህ ሁሉ መከፋፈልና ዘረኝነት ፍሬ ባለቤት የሆኑ ሁሉም የማይቀርላቸውን ዋጋ ይከፈላሉ። **አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም  ቢሆኑም ግን የተበላ እቁብ ሶስት ገጽታ ነገር አንድ ማንነት ከኢትዮጵያችን መወገድ ይገባዋል።** እያየነው ያለው እውነት የለማ ቡድንም፣ የጃዋር ተላላኪ ቡድንም የዳወድ ኢብሳ  ኦነግም የሚጣሉ የሚጋጩና  አንደኛው ሌላኛውን የሚሰድብ ወይም የሚነቅፍ ቢመስለንም አንድ እና አንድ መሆናቸውን ነው። **አንዲት ኢትዮጵያ ብሎ የዘር ፌደራሊዝም ፣ፍት ህ የተሞላባት ኢትዮጵያን እንገነባለን እያሉ አዲስ አበባ የእኛ ናት ማለት፣ የዜጎች  መብት የተከበረባት አገር**

**እንገነባለን እያሉ ከክልሌ ውጣልኝ ብሎ ማፈናቀል ኢትዮጵያዊ ልብስ ለብሶ ጎሰኝነትን ማሳደድ የቀን ቅዠት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን አለማወቅ ነው።** በእርግጥ ለእነ ዶክተር አብይ የረፈደ ቢመስልም በሃሰት ማንነት የተጀበነ ጎሰኝነት አይኑን አፍጥጦ ቢገለጥም ስህተትን የማስተካከያ ጊዜ ግን አለ። የአዲስ አበባ ወጣቶች አልተደራጁም ፣ ሌላው ኢትዮጵያዊም አልነቃም ፣ ትግሬዎችንም ወደ መቀሌ ልከናቸዋል፣ ዐማራውንም በዘረጋነው ድርጅታዊ ሰንሰለት አቅም አሳጥተነዋል በማለት የሚደረግ ስሌት ካለ ግን ዘመኑንም ህዝባችንንም አገራችንንም ካለማወቅ የመጣ ድንቁርና ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። በምርጫም ይሁን በሜጫ እናሸንፋለን ብሎ መነሳትም ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ እንደመውጣት ነው። ያለፉት ሶስት አስርት አመታት ያሳዩንና የተማርነው ታላቅ እውነት የመቶ ሚሊየን ህዝብ መኖሪያና ከሰማንያ በላይ ቋንቋ የሚነገርባት ኢትዮጵያ ከአሁን በኋላ የአንድን ጎሳ የበላይነት በመቀበል እየተገዛች እንደማትኖር ነው። አንድ ጎሳ ስለፈለገም የምትፈራርስ ኢትዮጵያ የለችም። እግዚአብሄር አገራችንን ይባርክ ።

መጋቢት 2011

አዲስ ተስፋ

addiste@gmail.com